## አዋጅ ቁጥር---/2014

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ

በኢትዮጵያ አስተማማኝ የዲጂታል የመታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት፤ ነዋሪዎች የመታወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥ፣ በመንግስት እና በግሉ ዘርፉ የአገልግሎት ሰጪና ተጠቃሚ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር ሥርዓትን ለመዘርጋት፣እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ፤

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገ፣ ዘርፍ ተሻጋሪ፣ መሰረታዊ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት፤ ሃገራዊ ልማትን በአግባቡ ለማቀድ፤ ምጣኔ ሃብታዊ ሽግግር ለመፍጠር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ፖሊሲዎች ሲቀረጹ እና የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን እና አካታች ያለመሆን ችግርን በቀላሉ በመለየት የሀብት ብክነትን በመቀነስ በነዋሪዎች መካከል ፍትሀዊነትን ለማስፈን የሚረዳ በመሆኑ፤

ጠንካራ፣ አስተማማኝ፣ ተደራሽ እና ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የኢትዮጵያ ዲጂታል የመታወቂያ መለያ ስርዓትን መዘርጋት ከወንጀል ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በመቀነስ ሃገራዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) እና (6) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር...../2014**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1."**የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት**" ማለት በኢትዮጵያ አንድን ነዋሪ በልዩ ሁኔታ በመለየት እና መታወቂያ መስጠት የሚያስችል የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃን መዝግቦ በአንድ ማእከላዊ ቋት በመያዝና ልዩ ቁጥር በመስጠት አገልግሎት የሚሰጥ አስተማማኝ የመታወቂያ ማረጋገጫ ስርዓት ነው፤

2."**ዲጂታል መታወቂያ**" ማለት በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ውስጥ ለተመዘገበ ሰው ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚሠጥ የራሱ መለያ ልዩ ቁጥር ያለው የመታወቂያ ዓይነት ነው፤

3."***መሠረታዊ መታወቂያ***" ማለት የአንድ ሰው መለያን በመጠቀም እንደ ልዩ ግለሰብ ለማረጋገጥ ህጋዊ መታወቂያ የሚሰጠውን መሠረታዊ አገልግሎት በአገር አቀፍ ደረጃ ለማግኘት የሚያስችል የመታወቂያ ዓይነት ነው፤

4."**ጊዜያዊ ዲጂታል መታወቂያ**" ማለት ዕድሜው በዲጂታል መታወቂያ ተቋም ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ሰው ያለ ባዮሜትሪክ ዳታ የሚሰጥ ጊዜያዊ የዲጂታል መታወቂያ አይነት ነው፤

5."**ባዮሜትሪክ**" ማለት የአንድ የተፈጥሮ ሰው ልዩ የሰውነት አካላዊ መለያዎች እና ስሌቶች የሆኑትን የጣት አሻራ፣ የአይን ብሌን፣ የፊት ገፅታ ምስል እና ሌሎች ልዩ መለያዎችን በመጠቀም የሰዎችን ልዩ መታወቂያ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፤

6."**ባዮሜትሪክ ዳታ**" ማለት ለዲጂታል መታወቂያ ዓላማ ተሰብስበው የተከማቹ አካላዊ የሆኑ የባዮሜትሪክ መረጃዎች ናቸው፤

7.**“ልዩ ቁጥር”** ማለት በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ውስጥ አንድን ሰው ከሌሎች ሰዎች ለመለየት የሚያገለግል ባዮሜትሪክ ዳታ ላይ በመመሥረት የሚሰጥ ሲሆን፤ ማንኛውም ተመዝጋቢ የምዝገባ ሂደቱን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቅ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚመነጭ ቋሚ የሆነ ለእያንዳንዱ ነዋሪ በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ እና ቁጥሩ ለግለሰቡ አንዴ ከተሰጠ ሊሻር የማይችል እና ለአንድ ተመዝጋቢ የህይወት ዘመን ሁሉ የሚያገለግል ቁጥር ነው፤

8.**“ተለዋጭ ቁጥር”** ማለት ከልዩ ቁጥር ጋር የተያያዘ በሚስጥራዊ ሁኔታ የተያያዘ ቁጥር ሲሆን፣ ከተመዝጋቢው በቀረበለት ጥያቄ መሠረት፣ የማረጋገጥ ተግባር ከተፈፀመ በኋላ የሚፈጠር ሆኖ ግለሰቦች ከተጠቃሚ አካላት ጋር ራሳቸውን ለመለየት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

9.**‘‘የዲጂታል መታወቂያ ተቋም”** ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበትን ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚያስተገብርና ይህንን አዋጅ የሚያስፈፅም መንግስታዊ አካል ወይም ተቋም ነው፡፡

10. **“ነዋሪ”** ማለት ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በአገሪቱ ህግ ፈቃድ አግኝቶ የሚኖር ወይም የሚሠራ ማንኛውም ሰው ነው፤

11. **“ተመዝጋቢ”** ማለት የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት መረጃውን በመስጠት ተመዝግቦ ልዩ ቁጥር የሚወስድ ሰው ነው፤

12. **“መዝጋቢ አካል”** ማለት የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም በተቋሙ በሚሰጥ ፈቃድ ወይም ውክልና መሠረት የተመዝጋቢን መረጃ የመሰብሰብ ሃላፊነት ያለበት አካል ነው፤

13. **“ተጠቃሚ አካል”** ማለት ከዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ከግለሰቡ በተሰጠ ፈቃድ እና መረጃ ላይ ተመስርቶ የግለሰብ ማንነትን የሚያረጋግጥ አካል ነው፤

14. **“ማረጋገጥ"** ማለት የዲጂታል መታወቂያ መረጃዎች ከተጠቃሚ አካል በሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጥ የማረጋገጥ ሂደት ነው።

15. **“የተመዝጋቢ መረጃ”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 የተጠቀሱት ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገቡ መረጃዎች ማለት ሲሆን የባዮሜትሪክ ዳታንም ይጨምራል፤

16. **"ፈቃድ"** ማለት ማንኛውም ተመዝጋቢ በነጻ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ፣ ጥርጣሬ በማያስነሳ መልኩ በመረጃ ላይ በመመሥረት በፅሁፍ ፣ በቃል ወይም በማናቸውም ግልጽ በሆነ መንገድ የተመዝጋቢ መረጃ እንዲቀናበር የሚሰጥ ስምምነት ነው፤

17. **“የመታወቂያ ካርድ”** ማለት የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥርና የተመዝጋቢ መረጃ የያዘ በቁሳዊ ወይም በዲጂታል አማራጭ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፤

18. **“የመታወቂያ ካርድ መረጃ”** ማለት በዲጂታል መታወቂያ ካርድ ላይ የሚታተም በዲጂታል አማራጭ የሚዘጋጅ ማንኛውም ፅሁፍ ነው፤

19. **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

20. **“መንግስት”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ የክልሎች አስተዳደርንም ያካትታል፤

21. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ሰው ማለት ነው፤

22. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ኢትዮጲያ ውስጥ ነዋሪ በሆነ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. ዓላማ

አዋጁ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1. ሁሉን አቀፍ፣ ወጥና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ፣ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበትን ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በመዘርጋት የተመዝጋቢዎችን መረጃዎች በመያዝ የዲጂታል መታወቂያ አጠቃቀም ስርዓትን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ፤

2. በመዝጋቢ አካላት ፥ በተጠቃሚ አካላት ፥ በአገልግሎት ሰጪና በተመዝጋቢ መካከል የሚኖር ግንኙነት እና መስተጋብር በእምነት እንዲዳብር የመተማመኛ ማዕቀፍን መዘርጋት።

3. የዲጂታል መታወቂያ ስርዓትን በሐገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገትና ተገማችነትን በማረጋገጥ ተጠያቂነትን፤ ግልፅነትን እና የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤

## 5. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ ተቋም

በዚህ አዋጅ የተጠቀሰውን አጠቃላይ የዲጂታል መታወቂያ አሰራር ስርዓት የተመለከቱ ጉዳዮችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ የሚወክለው የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ሃላፊነት ወስዶ፣ አዋጁን ይፈፅማል ፥ ያስፈፅማል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ምዝገባ እና አገልግሎት አሰጣጥ

## 6. የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አሰራር ስርዓትና መርሆች

1.የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ በዚህ አዋጅ በተዘረጉ የአሰራር ሥርዓቶች መሠረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፤

2.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩትን መረጃዎች አሟልቶ ለተመዘገበ ተመዝጋቢ የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር ከክፍያ ነጻ ይሰጣል።

3.ማንኛውም በኢትዮጲያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ሰው ተመዝግቦ የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት የማግኘት መብቱን የሚያረጋግጥ ስርዓት ነው፤

4.የሌሎች ማናቸውም የነዋሪ መለያ መረጋገጥ ለሚጠይቁ ተግባራት ማረጋገጫ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል በሚያስችል አግባብ የሚደራጅ ስርዓት ነው፤

5.በሐገሪቱ የሚገኙ ተጠቃሚ አካላት፣ የነዋሪ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የባዮሜትሪክ እና የዲጂታል መለያ ስርዓትን በሚዘረጉበት ጊዜ ከዲጂታል መታወቂያ የቴክኖሎጂ ስርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር ይኖርበታል፤

6.ለዜጎች የግል መረጃ ጥበቃ ደህንነት ሲባል የዲጂታል መታወቂያ ተቋም በዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ውስጥ ያለው መረጃ በዚህ ሕግ ውስጥ በተገለጸው ዓላማ መሠረት ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለበት።

7.ሁሉን አቀፍ፣ አመኔታ የሚጣልበት እና ህጋዊ መሠረት ያለው የነዋሪ ግለሰቦችን ልዩ መለያ ማረጋገጫ ስርዓት በመዘርጋት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችን ደህንነት፥ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እና ተደራሽነትን ለማስፋት መሠረት ሆኖ ያገለግላል፤

8.በመንግስት ለሚሰጡ የነዋሪነት መታወቂያ፥ የወሳኝ ኩነት መረጃዎች እና ሌሎች የግለሰብ ልዩ መታወቂያ አገልግሎቶች መሠረት በመሆን ያገለግላል፤

9.የመሠረታዊ መታወቂያ አገልግሎትን ለመስጠት የሚሰበሰቡ የባዮሜትሪክ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥልጣን የዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም ተቋሙ የፈቀደለት አካል ብቻ ነው።

10. ለመንግስት እና ለአመራር ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ የዴሞግራፊክ ስርዓት በመዘርጋት ፥ ልዩ ልዩ የዜጎችንና በሀገሪቱ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን መረጃ አደራጅቶ ለመያዝ በሚያስችል መልኩ ይቋቋማል።

## 7. በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚመዘገቡ መረጃዎች

1.ግለሰባዊ ማንነትን ፥ ነዋሪነትን ወይም የመኖርያ አድራሻን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ ሰነዶች እና ሌሎች ተቀባይነት ባላቸው የሰነድ ወይም የሰው ምስክር ማስረጃዎች በመጠቀም የተመዝጋቢ መረጃ ልዩ መሆኑን በጥንቃቄ በማረጋገጥ ይመዘግባል።

2.ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን፤ በአሳዳጊ ወይም በሕጋዊ ሞግዚት በኩል ተመዝግቦ ልዩ ቁጥር ያለው ጊዜያዊ ዲጂታል መታወቂያ ሊያገኝ ይችላል።

3. ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

ሀ. ስም ፥ የአባት ስም ፥ የአያት ስም ፤ ወይም ነዋሪ ለሆኑ የውጪ ዜጎች የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ወይም የመጀመሪያ፣ መካከለኛ እና የመጨረሻ ስም፤

ለ. የትውልድ ቀን፣ወር እና ዓመት፤

ሐ. ፆታ ፤

መ. መኖሪያ አድራሻ፤

ሠ. ዜግነት፤ የዜግነት ማረጋገጫ ሰነድ ላላቸው ኢትዮጵያውያን ወይም የውጭ አገር ዜጎች ዜግነት የሚመዘገብ ሲሆን ፤ ማረጋገጫ ለሌላቸው ነዋሪዎች "ያልተረጋገጠ" በሚል ይመዘገባል።

4.ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚከተሉትን መረጃዎች በተጨማሪነት ሊይዝ ይችላል፦

ሀ. ስልክ ቁጥር፤

ለ. የኢሜይል አድራሻ፤

ሐ. ፖስታ  አድራሻ

5.በልዩ ሁኔታ የሚጠየቁ መረጃዎች፡-

ሀ. ዕድሜው በተቋሙ ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን የወላጅ ፥ የአሳዳጊ ወይም ህጋዊ ሞግዚት ልዩ ቁጥር፤

ለ. የተመዝጋቢ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፣ መሰረት የተዘረዘሩ የመታወቂያ ሰነድ ማስረጃዎች ማቅረብ በማይችልበት ጊዜ ፤ ልዩ ቁጥር የተሰጠው አንድ የሰው ምስክር ይዞ መቅረብ አለበት፤

6.ባዮሜትሪክ ዳታ፡-

ሀ. ለአካለ መጠን ላልደረሰ ዕድሜው በመመሪያ ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነ ህጻን ባዮሜትሪክ ዳታ መስጠት ግዴታ አይሆንም፤

ለ. የፊት ገፅታ ፎቶግራፍ አስገዳጅ ባዮሜትሪክ ዳታ ሲሆን ፤ በአካል ጉዳት ምክንያት ተመዝጋቢው ሌሎች ባዮሜትሪክ መረጃዎችን መስጠት አለመቻሉ ከተረገገጠ፣ መውሰድ የሚቻሉትን የባዮሜትሪክ ዳታ ብቻ መሰብሰብ ይቻላል፤

ሐ. በጤና ሁኔታ ልዩ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ከተረጋገጠ ዲጂታል መታወቂያ ተቋም ባዮሜትሪክ ለመቀበል በሚችሉበት መልክ ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፤

መ. ባዮሜትሪክ ዳታ በድጋሚ መታደስ ይኖርበታል፤

## 8. ስለ ልዩ ቁጥር <u>አሰጣጥ</u>

1. የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር ከመስጠቱ በፊት መዝጋቢው ለመመዝገብ ሰው ልዩ ቁጥር አለመውሰዱየቀረበው ን ማረጋገጥ አለበት።

2. የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩት መረጃዎች ተመዝግበው ወደ ስርዓቱ ከገቡ በኋላ፣ አንድ ሰው ከሌላ ሰው በልዩነት እና በአስተማማኝነት ለመለየት የሚያስችል ልዩ ቁጥር ለእያንዳንዱ ተመዝገቢ ይሰጣል፤

3. ልዩ ቁጥሩ ኤሌክትሮኒክ በሆነ ስርዓትና በሚስጥራዊ መንገድ የሚመነጭ ሲሆን ከቁጥሩ ጀርባ ያለውን ዝርዝር መረጃ እና ግላዊነት የሚጠብቅ ይሆናል።

4. አንድ ልዩ ቁጥር ለአንድ ተመዝጋቢ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ፤ ይህ ልዩ ቁጥርም ለህይወት ዘመን ለተመዘገበው ሰው የማይቀየር ይሆናል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ልዩ ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዘርፎች በተለየ መልኩ ወይም በተመዝጋቢው ፍላጎት መሰረት ልዩ ቁጥሩን ተክቶ መስራት የሚችል ተለዋጭ ቁጥር መስጠት ይቻላል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ልዩ ቁጥር ወይም ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ የተጠቀሰው ተለዋጭ ቁጥር ለተመዝጋቢው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የሚሰጠው ዲጂታል መታወቂያ ካርድ ላይ መጠቀስ አለበት።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ልዩ ቁጥር የማይለወጥ ሲሆን፣ የተመዝጋቢውን የመረጃ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በካርድ ላይ የሚታተመውና በሌሎች ሁኔታዎች ጥቅም ላይ የሚውለው ቁጥር ግን እንደየሁኔታው በሚቀያየር ሚስጥራዊ ተለዋጭ ቁጥር ሊተካ ይችላል።

8. የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር የጠፋበት ማንኛውም ሰው ልዩ ቁጥሩ ስለመጥፋቱ ለዲጂታል መታወቂያ ተቋም ወይም ተቋሙ ለወከለው አካል በአካል ቀርቦ ቁጥሩን መልሶ ማግኘት ይችላል።

9. ማንኛውም ሰው ልዩ ቁጥሩን አንዴ ከወሰደ በኋላ፤ በስህተት ወይም ሆነ ብሎ ዳግም ለመመዝገብ ቢሞክር ፤ ዲጂታል መታወቂያ ተቋም የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም የመከልከል ወይም ሌሎች የህግ እርምጃዎች የመውሰድ ሃላፊነት አለበት።

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በተመዝጋቢው ፍላጎት ፥ በሞት ምክንያት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የዲጂታል መታወቂያ ልዩ ቁጥር ሊቆለፍ ወይም ከሥራ ውጪ እንዲሆን ሊደረግ ይቻላል ፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ የሚወሰን ይሆናል።

## 9. ስለ ቋንቋ

1.በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚመዘገቡ መረጃዎች በፌዴራል የሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይሆናል።

2.የዲጂታል መታወቂያ መረጃው የሚመዘገብበት ክልል ከፌዴራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ የተለየ ከሆነ ፤ በክልሉ የሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ ይሆናል፡፡

3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተገለጸው ከፌዴራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚመዘገቡ መረጃዎች በግለሰቡ ፍላጎት በመረጠው ተጨማሪ ቋንቋ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

4.የዲጂታል መታወቂያ ካርድ መረጃ ላይ የሚወጡት ፅሁፎች እና መረጃዎች በፌዴራል የሥራ ቋንቋ ወይም የተለየ ከሆነ በክልሉ የሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዘኛ መሆን አለባቸው።

5.የሚታተመው የዲጂታል መታወቂያ ካርድ ላይ መረጃ የሚገለጽበት ቋንቋ በተመለከተ የአገሪቱን ህግ መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

## 10. ስለ ዲጂታል መታወቂያ የመረጃ ለውጥ

ማንኛውም ሰው የዲጂታል መታወቂያ በያዛቸው መረጃዎች ወይም ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በገቡ መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲኖር ማሳወቅ አለበት፤

## ክፍል ሶስት
## ስለ ዲጂታል መታወቂያ የማረገገጥ አገልግሎት እና ተጠቃሚ አካላት

### 11. ስለ ዲጂታል መታወቂያ ማረጋገጥ አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም

1.ያለተመዝጋቢ ፍቃድ የዲጂታል መታወቂያ ማረጋገጥ ስራዎች በማንኛውም ሁኔታ መፈቀድ አይችሉም።

2.በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ውስጥ ያልተመዘገቡ ግለሰቦችን ማንነት ለማረጋገጥ የሚረዱ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ፣ አገልግሎት ለመስጠት ግለሰቡ የዲጂታል መታወቂያ ያለው መሆኑን አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ሊያደርግ ይችላል።

3.ማንኛውም የዲጂታል መታወቂያን የያዘ ሰው ግላዊ ማንነቱን ለማስረዳት ወይም ለማረጋገጥ እንደ ህጋዊ እና በቂ ማስረጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

4.በኢትዮጲያ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ነዋሪ የዲጂታል መታወቂያ ላይ የተመሰረተ የማረጋገጥ አገልግሎት ለማግኘት ልዩ ቁጥር ወይም ልዩ ቁጥሩን የያዘ መታወቂያ ካርድ መያዝ አለበት።

### 12. ስለ ዲጂታል መታወቂያ ተጠቃሚ አካላት

1.ተጠቃሚ አካላት በተመዝጋቢው ፈቃድ ላይ ተመስርተው የግለሰብ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ከተቋሙ ወይም ተቋሙ ከወከለው አካል ማግኘት ይችላሉ።

2.ማንኝውም ተመዝጋቢ፣ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲያስፈልግ፣ በተጠቃሚ አካላት በኩል ዲጂታል መለያን የማረጋገጥ አገልግሎት ማግኘት ይችላል።

3.ተጠቃሚ አካላት የማረጋገጥ አገልግሎት ከማግኘታቸው በፊት ከተቋሙ ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## ክፍል አራት

## የዲጂታል መታወቂያ መረጃ አስተዳደር ፥ እድሳት እና የመታወቂያ ካርድ

### 13. የዲጂታል መታወቂያ መረጃ አስተዳደር

1.ተቋሙ የተመዝጋቢ መረጃዎችን በጠንካራ የዲጂታል መታወቂያ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ያስተዳድራል።

2. የዲጂታል መታወቂያ ተቋም በጊዜ ሂደት የሚለዋወጡ የዲጂታል መታወቂያ መረጃዎችን የማዘመን፣ እንደገና የማረጋገጥ፣ የማደስ፥ በጊዜያዊነት የመቆለፍ ወይም የመሻር ሥራዎችን ይሠራል፡፡

### 14. ስለ ዲጂታል መታወቂያ መረጃ መጭበርበር ወይም መሳሳት

1.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የአንድ ሰው ዲጂታል መታወቂያ የተጭበረበረ መሆኑ በተቋሙ ከተረጋገጠ ፤ መረጃውን ሊያስተካክል ፥ ዲጂታል መታወቂያውን ተቋሙ ሊቆልፍ እናም ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

2.በስህተትም ሆነ ሆን ተብሎ የገባ የተሳሳተ መረጃ መኖሩ ሲረጋገጥ ፤ ልዩ ቁጥሩ ሳይቀየር መረጃውን የማስተካከል ሃላፊነት ተቋሙ አለበት።

### 15. የህዝብ ተሳትፎ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

**1.**ተቋሙ ከሕዝብ እና ተጠቃሚ አካላት ዲጂታል መታወቂያ አሰራር ስርዓት ሂደት ውስጥ መሳተፍ የሚችሉበት ቋሚ ስርዓት ይዘረጋል።

**2.**ተቋሙ በኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አሰራር ስርዓት ሂደት ለሚያጋጥሙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች የቅሬታና የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት ዝርዝር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

**3.**በተቋሙ የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ አካል ቅሬታውን በመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

## 16. <u>ስለ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ</u>

1.በዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ውክልና በተሰጣቸው አካላት የሚሰጥ ማንኛውም አይነት የዲጂታል መታወቂያ ካርድ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ ከሀ እስከ መ የተዘረዘሩት መረጃዎች በሙሉ ፤

ለ. ፎቶግራፍ ፤

ሐ. ልዩ ቁጥር ወይም ተለዋጭ ቁጥር ፤

መ. መታወቂያው የተሰጠበት እና የሚያበቃበት ቀን፤

ሠ. እና ሌሎች በመመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮች የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡፡

2.ማንኛውም ሰው የዲጂታል መታወቂያ ካርድ የእድሳት ዘመን ባለፈ ጊዜ ወይም የባዮሜትሪክ ዳታ ዳግም ሲወሰድ፣ የዲጂታል መታወቂያ ካርድ መታደስ አለበት፡፡

3.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የዲጂታል መታወቂያ ካርድ በተቋሙ ወይም በወከላቸው አካላት በነፃ ወይም በክፍያ ሊሰጥ ይችላል።

4.ዲጂታል መታወቂያ ተቋም፣ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ በሚያድስበት ጊዜ ቀድሞ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነታቸውን እና የተመዝጋቢውን ማንነት ትክክለኛነት አረጋግጦ የማደስ ግዴታ አለበት።

5.ዲጂታል መታወቂያ ካርድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው መታወቂያው ስለመጥፋቱ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ፤ ወይም የተበላሸውን መታወቂያ በማያያዝ ፤ በምትኩ ዲጂታል መታወቂያ እንዲሰጠው ለተቋሙ በማመልከት የተቋሙን አሰራር ተከትሎ መውሰድ ይችላል።

6.በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ልዩ ቁጥሩ የተቆለፈበት ሰው የመታወቂያ ካርዱን ለተቋሙ መመለስ አለበት።

7.ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው መረጃ እንደደረሰው የጠፋው ዲጂታል መታወቂያ ካርድ መጥፋቱን በማዕከላዊ መረጃ ቋት መመዝገብ አለበት።

8.የዲጂታል መታወቂያን ተጠቅሞ የሚከናወኑ የማጭበርበር ተግባራት የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ ስለሚሆኑ፣ ዲጂታል መታወቂያ ካርድ ወድቆ ያገኘ ማንኛውም ሰው መታወቂያውን ወዲያውኑ ለተቋሙ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ማስረከብ አለበት።

# ክፍል አምስት
# የዲጂታል መታወቂያ የግለሰብ መረጃ ደህንነት እና ጥበቃ

## 17. የ<u>ግለሰብ</u> መረጃ አያያዝና ደኅንነት

1.ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰቡ የግለሰብ መረጃዎች፣ ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ አኳኋን በሥርዓት ተደራጅተው ዲጂታል መታወቂያ ተቋም በሚያስተዳድረው የመረጃ ቋት ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

2. ዲጂታል መታወቂያ ተቋም የያዛቸውን መረጃዎች ከተለያዩ የተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ፣ የኤሌክትሮኒክ መንገዶችን በመጠቀም ከሚደርሱ ጥቃቶች ፣ ከስርቆት ፥ መጭበርበር እና መሰል የወንጀል ጥፋቶች ለመጠበቅ የሚያስችል ደህንነቱን የጠበቀ ስርዓት በመዘርጋት የህዝብን መረጃ መንከባከብ አለበት።

3. በዲጂታል መታወቂያ አሰራር ስርዓት ውስጥ የግል ዳታ ስርቆት፥ ጥፋት እና ውድመት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የቴክኒክና የደህንነት አሰራሮች በተቋሙ ሥራ ላይ መዋል አለበት።

4. የግላዊነት የቴክኒክ ቁጥጥር ማእቀፍ ከሕግ ቁጥጥር ማዕቀፉ ባልተናነሰ ደረጃ ለመረጃ ደህንነት እና ጥበቃ ከለላ መሆን አለበት።

## 18. የተመዝጋቢ መረጃ ጥበቃ

1.ዲጂታል መታወቂያ ተቋም በህገመንግስቱ እና ሐገሪቱ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎች መሠረት ከሚፈቀደው ውጪ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገቡ መረጃዎችን በመሰብሰብ በመመዝገብ በማረጋገጥ እና ይዞ በማቆየት ሂደት ባሉ ተግባራት ውስጥ የተመዝጋቢ መረጃዎች ሚስጢራዊነት መጠበቅ አለበት።

2.ለዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሰዎችን በልዩ መለያ ለመለየት የግዴታ የሚያስፈልጉና ስርዓቱን በቀጥታ ከሚደግፉ በስተቀር ሌሎች ትርፍ መረጃዎች በዲጂታል መታወቂያ ተቋም መሰብሰብ የለባቸውም።

3.በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተሰበሰበ ማንኛውም የተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ባለቤት ተመዝጋቢው በመሆኑ፣ በማንኛውም የዲጂታል መታወቂያ አሠራር ስርዓት ውስጥ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረጉ የማረጋገጥ ተግባራት በተመዝጋቢው ፈቃድ ብቻ ሊደረጉ ይችላሉ።

4.በማንኛውም ሰው ፥ የህግ አስከባሪ ወይም የደህንነት ተቋም ተመዝጋቢ ፈቃዱን በግልጽ ሳይሰጥ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የተመዘገቡ የግል መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መግለጽ፣ ማሰራጨት፣ ማተም፣ መጠቀም፣ መረጃውን መስጠት ወይም ቅጂውን ለሶስተኛ ወገኖች ወይም አካላት መስጠት ወይም ይፋ ማድረግ አይቻልም፡፡

5.አሰራርና ህግን ጠብቆ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ለተሰበሰበ የማንኛውም ተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ያለ ተመዝጋቢው ፈቃድ ለሌላ ሰው መግለጽ ፣ ማስተላለፍም ሆነ እንዲለወጥ መፍቀድ ለዲጂታል መታወቂያ ተቋሙ አይፈቀድም።

6.በህግ ለተፈቀደላቸው አካላት ግላዊ መረጃን የማያጋልጡ የተጨመቁ ዲሞግራፊክ ሪፖርቶች እና የስታትስቲክስ መረጃዎችን ተቋሙ በነፃም ሆነ በክፍያ መስጠት ይችላል።

7.ከዲጂታል መታወቂያ ቋት አሰራሩን ጠብቆ ለተጠቃሚ አካላት የማረጋገጥ ሥራ አንድ ጊዜ የተላለፈው የተመዝጋቢ መረጃ ለዚያ ነጠላ አገልግሎት ብቻ ነው ጥቅም ላይ ሊውል ወይም ሊያገለግል የሚችለው።

8.አንዴ የተጋራን የተመዝጋቢ መረጃ ለተጨማሪ ጊዜ በመረጃ ቋት ውስጥ ማስቀመጥ እና መጠቀም መረጃን እንደማረጋገጥ ተግባር ተደርጎ አይቆጠርም።

9.ተጠቃሚ አካላት አንዴ የተጋራን የተመዝጋቢ መረጃ እስከፈለጉ ጊዜ ድረስ ከራሳቸው ማቆየት ይችላሉ ፤ ሆኖም ይህንን መረጃ እንደ የማረጋገጫ ምንጭ አድርገው ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች አካላት በድጋሚ መጠቀም አይችሉም።

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ፥ (7) እና (8) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠቃሚ አካላት በተመዝጋቢው ፈቃድ ያገኙትን መረጃ ፥ መረጃውን ከወሰዱበት አላማ ውጪ ለራሳቸውም ሆነ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በወንጀል ያስጠይቃል።

11. በምዝገባ ወቅት በዲጂታል መታወቂያ ተቋም የሚዘጋጅ የተመዝጋቢውን ሙሉ ፈቃድ ፥ መብት እና ግዴታዎች የሚገልፅ የፈቃደኝነት ቅፅ በተመዝጋቢው መሞላትና መፈረም አለበት።

12. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በምዝገባ ወቅት ለተመዝጋቢ ምስክር ሆነው ለሚቀርቡ ሰዎች በተቋሙ የሚዘጋጅ የምስክሩን ሙሉ ፈቃድ ፥ መብት እና ግዴታዎች የሚገልፅ የፈቃደኝነት ቅፅ በምስክር መሞላትና መፈረም አለበት፤ የምስክሩ ልዩ ቁጥር በቅጹ ላይ መሞላት እና በድጂታል መታወቂያ ስርዓቱ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) እና (11) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ማንኛውም አገልግሎት ሰጪዎችም ሆኑ ተጠቃሚ አካላት ለሚሰጡት አገልግሎት ዲጂታል መታወቂያን እንደ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የሚያደርግ አሠራር መዘርጋት ይችላሉ።

14. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በተመዝጋቢው ፈቃዱን ሲሰጥ መረጃው ይፋ መደረግ ይችላል።

15. በህገ-ወጥ መንገድ ይፋ በመደረጉ ምክንያት የተገኘ ማንኛውም መረጃ በማንኛውም የፍትህ ፣ የዳኝነት ወይም የአስተዳደር ሂደቶች ተቀባይነት የለውም።

## 19. የወንጀል ተጠያቂነት

1.በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎችን አለመፈጸም የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡

2.በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ ወቅት ሆነ ብሎ ከቅን ልቦና ውጭ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም እውነተኛውን መረጃ የደበቀ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በሃሰት በተዘጋጀ ወይም በተጭበረበረ የዲጂታል መታወቂያ የተጠቀመ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) የዲጂታል መታወቂያና ልዩ ቁጥርን አስመስሎ የሠራ ፥ የተጠቀመ ወይም ወደ ሃሰት የለወጠ እንደሆነ፤ ወይም

መ) የዲጂታል መታወቂያን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ይዘት የለወጠ፣ ያሻሻለ፣ የሰረዘ፣ የግል ዳታ ባለቤትነት መብትን ያላከበረ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ወደ ሃሰት የለወጠ፤ ወይም

ሠ) የዲጂታል መታወቂያን አስመልክቶ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ጉዳት ያደረሰ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያደረገ፣ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የወሰደ እንደሆነ፤ ሰባት ዓመት በማያንስ እና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ በማያንስና ከብር አምስት መቶ ሃምሳ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

3.በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 2 የተፈጸመው ጥፋት ከዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት፣ ወይም ለመመዝገብ ወይም ለማረጋገጥ፣ ሥልጣን በተሰጠው አካል፣ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ፣ ወይም የተጠቃሚ አካል ሠራተኛ ወይም ኃላፊ መሆኑ ከተረጋገጠ ጥፋተኛው ከአስር ዓመት እስከ አስራ አምስት አመት ጽኑ እስራት እና ከብር ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ በማያንስና ከብር አንድ ሚሊዮን፣ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የአዋጁ ዓላማ እንዲሳካና ዲጂታል መታወቂያ ተቋም በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መፈጸም እንዲችል የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 21. የተሻሩ ሕጎች

1.የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 ከአንቀጽ 55 እስከ 62 ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ 804/2005 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 11 እና ሌሎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ የብሔራዊ መታወቂያን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

2.የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 22. *ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*

1.የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

2.የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ የሚወክለው የዲጂታል ተቋም ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም በሚያስፈልጉ በሚከተሉት እና በሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡-

ሀ. የዳግም ምዝገባ ቅጣትን በተመለከተ፤

ለ. የተመዝጋቢን የመረጃ ደህንነት ለመጠበቅ የሚቀያየረውን ሚስጥራዊ ተወካይ ቁጥር ሊተካ ስለሚችልበት ሁኔታ፤

ሐ. አንድ ተመዝጋቢ ከሌላ ተመዝጋቢ በልዩነት እና በአስተማማኝነት ለመለየት የሚያስችል ልዩ ቁጥር ስለሚሰጥበት የባዮሜትሪክ ዳታ ይዘት እና ተያያዥ ዝርዝር አሠራሮች፤

መ. ከዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ፣ ማረጋገጥ፣ መጠቀም፣ ማስተዳደር እና ሌሎች አገልግሎቶችን፤ በውክልና ለተጠቃሚ፥ ለመዝጋቢ እና ለሌሎችም አካላት መስጠት ስለሚቻልበት ዝርዝር ሁኔታዎች ፤

ሠ. ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን የወላጅ፥ የአሳዳጊ ወይም ህጋዊ ሞግዚት በልዩ ሁኔታ ልዩ ቁጥር ስለሚሰጥበት አግባብ፤

ረ. ዕድሜው ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን ባዮሜትሪክ ዳታ መስጠት ግዴታ ስለማይሆንባቸው ጉዳዮች፤

ሰ. በአካል ጉዳት ምክንያት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባዮሜትሪክ መረጃ መስጠት አለመቻሉ ከተረገገጠ ፥ መውሰድ የሚቻሉት የባዮሜትሪክ ዳታ አሰባበሰብ በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ሸ. በጤና ሁኔታ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ዲጂታል መታወቂያ ተቋም ባዮሜትሪክ ለመቀበል በሚችሉበት መልክ የህክምና ማስረጃ ተቀብሎ ተቀብሎ ፤ ጊዜያዊ መታወቂያ ሊሰጣቸው ስለሚችልባቸው ጉዳዮች፤

ቀ. ባዮሜትሪክ ዳታ በድጋሚ መታደስ ስለሚኖርብት የጊዜ ገደብ፤

በ. ዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት ለመቀበል ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን ፤ በአሳዳጊ ወይም በሕጋዊ ሞግዚት በኩል ተመዝግቦ ልዩ ቁጥር ያለው ጊዜያዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲያገኝ ዕድሜው ገደብ ስለሚወሰንበት ሁኔታ ፥

ተ. የዲጂታል መታወቂያ በያዛቸው መረጃዎች ወይም ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በገቡ መረጃዎች ላይ ለውጥ ማሳወቅና መረጃውን ማስተካከል በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ቸ. የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን አቀራረብና አፈታት በተመለከቱ ጉዳዮች፤

ነ. በዲጂታል መታወቂያ ተቋም እና ውክልና በተሰጣቸው አካላት የሚሰጥ የዲጂታል መታወቂያ ካርድ ስለሚይዛቸው መረጃዎች እና ሌሎች በምዝገባ ጊዜ የተወሰዱ መረጃዎች ህትመት ስለሚወሰንበት አግባብ፡፡

ኘ. የዲጂታል መታወቂያ ካርድ የሚያገለግልበት ጊዜ ስለሚወሰንበት አግባብ ፤

አ. በልዩ ሁኔታ ዕድሜው በዲጂታል መታወቂያ ተቋም ከተወሰነው ዓመት በታች ለሆነ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ህጻን የወላጅ ፥ የአሳዳጊ ወይም ህጋዊ ሞግዚት ልዩ ቁጥር ስለሚሰጥበት ዝርዝር አፈጻፀም በተመለከተ፤

ከ. የተመዝጋቢዎችን መደበኛ መኖሪያ ቦታ በተመለከተ አካታች እንዲሆን ስለሚወሰንባቸው ሁኔታዎች ፤

ኸ. የባዮሜትሪክ መረጃ በአካል ጉዳት ምክንያት መስጠት የማይቻልባቸውን አግባብ በተመለከቱ ጉዳዮች፤

ወ. በስህተት ወይም ሆነ ተብሎ የገባ የተሳሳተ መረጃ ልዩ ቁጥሩ ሳይቀየር ህጋዊ መንገዱን ተከትሎ መረጃውን ማስተካከል ስለሚቻልበት አግባብ፤

## 23. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ..... ቀን 2014 ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

ረቂቅ ሰነድ